መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

አቋማቸውን ያልቀየሩ ሰዎች።

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሳሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ንጉስ ናቡከደነጾር ትልቅ ምስልን
አቆመ። ከእግር እስከራሱ ድረስ
ከወርቅ የተሰራ ነበረ። ምንአልባት
ንጉሱ ወርቃማው የንግስና ዘመኑ
እንደሚያበቃት የነገረውን ረስቶታል።
ምንአልባት ሙሉ ለሙሉ ከወርቅ
የተሰራ ምስል ከሰራ ፣ በሕልሙ
በኩል የተገለጠው የእግዚአብሔር
ቃል እውነት አይሆንም ይሆናል።

ከንጉሱ አገልጋዩች መካከል የሆነ
አንድ ሰውም ለሁሉም ሰው
የወጣውን ትዕዛዝ አነበበ
፤”በወርቃማው ምስል እግር ስር
ሁላችሁም ወድቃችሁ
ትሰግዳላችሁ ፤ ለዚያ ምስል
ያልሰገደ ሁሉ ለሚቃጠለው እሳት
እንዲጣል ተላልፎ ይሰጣል።”

3

ከሶስቱ ወጣቶች የተቀረው ሁሉ ሰው ይሄንን አደረገ ፤ እነዚህ ሶስት ሰዎች ዕብራዊያን ነበሩ። እነርሱም የዳንኤል ወዳጆች የሆኑት ሲድራቅ ፣ ሚሳቅና አብድናጎ ነበሩ። በጊዜው ዳንኤል አብሯቸው ያለ አይመስልም ነበረ ፤ በእርግጠኝነት ግን እርሱም ቢሆን ሰው ለሰራው ምስል በፍጹም አይሰግድም ነበረ።

4

የንጉሱ ጠቢባን በዳንኤልና በጓደኞቹ እጅግ ይቀኑ ነበረ ፤ ምክንያቱም ፣ ንጉሱ ወዶቸዋልና። ስለዚህ እነርሱም እንዲህ አሉ ፣ “በባቢሎን አውራጃ ላይ አለቃ እንዲሆኑ አድረገህ የሾምካቸው ሶስት ሰዎች አሉ ፤ ሲድራቅ ፣ ሚሳቅ እና አብድናጎ ። እነዚህ ሰዎች፣ ንጉስ ሆይ አንተን አይታዘዙህም። ለአንተ አይሰግዱም ፤ ላቆምከውም የወርቅ ምስል።”



5

ንጉስ ናቡከደነጾርም በቁጣ ተሞላ ። አስጠነቀቃቸውም ፣ “ካልሰገዳችሁ ፣ በሚነድደው እሳት ውስጥ ትጣላላችሁ። የቱኛው አምላክ ከእጄ ሊያስጥላችሁ ይችላል?”

6

ንጉሱ ታላቅ ስሕተት እየሰራ ነበረ። ሕያው አምላክን እየተገዳደረ ነበረ። ሶስቱ ዕብራዊያን ወጣቶች ፣ ለቆመ ምስል መስገድ እግዚአብሔርን መበደል እንደሆነ ያውቁ ነበረ። ቆመውም ቀሩ ። እግዚአብሔርን ስለታመኑ ፣ ንጉሱን አልፈሩትም ነበረ።



7

እነዚህ ሶስት ጠቢባን ለንጉሱ የሚሰጡት መልስ ነበራቸው። እንዲህም አሉ ፣ “እኛ የምናመልከው አምላክ ከሚቃጠለው እሳት ያድነናል ፤ ባያድነንም ፣ ይሄንን እንድታውቅ እንወዳለን ፤ ንጉስ ሆይ ለአንተ አማልክትም ሆነ ላቆምከው ምስል ፈጽሞ አንሰግድም።”



8

ንጉስ ናቡከደነጾርም
እጅግ ተበሳጨ! ከዚህ
አስቀድሞ ከሚነደው
ይልቅ ሰባት እጥፍ
ይነድድ ዘንድ አዘዛቸው::
አሁንም ግን ሰዎቹ
አልሰገዱም::



9

ንጉሱም ከሰራዊቱ መካከል ያሉ ኃያላን ሰዎችን አዘዛቸውና ፣
ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎን አስረው በሚቃጠለው እቶን
ውስጥ እንዲጥሏቸው
አዘዛቸው::

10

እሳቱ እጅግ የሚያቃጥል ነበረና ፣
ሲድራቅ ፣ ሚሳቅንና አብድናጎን
የጣሏቸው ሰዎች በእሳቱ ወላፈን
ተቃጥለው ሞቱ::

11

ንጉሱ አመቺ ከሆነ ርቀት ሆኖ ይከታተል ነበረ:: ሶስቱ ሰዎች ወደ
ሚቀጣጠለው እሳት ውስጥ ተጥለው ሲገቡ አያቸው:: ነገር ግን ፣
ይሔንን ብቻ አልነበረም የሚከታተለው::

12

ንጉስ ናቡከደነፆር እጅግ ተደነቀ! ረዳቶቹንም እንዲህ
ሲል ጠየቀ ፣ “ሶስት ሰዎችን ወደ እቶኑ እሳት
ጥለናቸው አልነበረም ;” እነርሱም
“አዎ!” ብሎ መለሱለት::
እርሱም ፣ “ተመልከቱ !
አራት የተፈቱ ሰዎችን ነው
የማየው ፤ በእሳቱ መካከል
ቢያልፉም ምንም
አልተጎዱም ::
አራተኛው ሰውም
የእግዚአብሔርን
ሰው ይመስላል::”

13

ወደ ሚቃጠለው የእቶኑ እሳት እየተጠጋ ንጉሱ
እንዲህ ሲል ጮኸ ፣ “ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣
አብድናጎ ፣ የኃያሉ አምላክ አገልጋዮች ፣ ኑ!
ውጡ::” ሲድራቅ ፣ ሚሳቅና አብድናጎም
ከእቶኑ እሳት ውስጥ ወጡ::

14

ሁሉም ሰዎች በዚያ ተሰበሰቡ እና ሶስቱን ዕብራዊያን ይፈትኗቸው ነበረ፡፡ እነርሱን ያቃጥላቸው ዘንድ እሳቱ ኃይል እንደሌለው አዩ፡፡ ጸጉራቸው አልተነዳም ፣ ልብሳቸውም አልተቃጠለም ነበረ፡፡ የእሳት ሽታ እንኳን እነርሱ ላይ አልቀረም ነበረ፡፡

ምን እንደተከሰተ ባወቀ ሰዓት ፣ ንጉስ ናቡከደነጾር ጥበበኛ የሆነን ነገር አደረገ፡፡ ጸለየ ፣ እና እንዲህ አለ ፣ “አገልጋዮቹንና በእርሱ የሚታመኑትን ሁሉ መልዓኩን ልኮ ያዳናቸው የሲድራቅ ፣ የሚሳቅ እና የአብድናጎ አምላክ የተባረከ ነው፡፡”



አቋማቸውን ያልቀየሩ ሰዎች፡፡

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዳንኤል 3

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሳልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሰማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። አባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል እንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16